# የአማራ ሴቶች ማህበር

# የተሻሻለ

# ሕገ-ደንብ

ግንቦት 2014 ዓ.ም

ባህርዳር

## መግቢያ

ሴቶች ሰው በመሆናቸው የተጎናጸፏቸው ሰብዓዊ መብቶች እና ነጻነቶች እንዳይገሰሱ እና እንዳይጣሱ ለመጠበቅ የሚያስችሉ በዓለም-አቀፍ እና አሕጉር አቀፍ ደረጃ መግለጫዎች፣ ስምምነቶች እና መርሆዎች እየወጡ በሥራ ላይ እንዲውሉ ከመደረጋቸውም በላይ እራሳቸውን የቻሉ ያታ ተኮር ልዩ ልዩ መግለጫዎች፣ ስምምነቶች እና ፕሮቶኮሎች እንዲሁም የማስፈጸሚያ ስልቶች ወጥተዋል፡፡ ከእነዚህም አብዛኞቹን አገራችን ኢትዮጵያ ተቀብላ በማጽደቅ የሕጎቿ አካል ከማድረጓም በላይ እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት አድርገው የወጡ እና ተግባራዊ በመሆን ላይ የሚገኙ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ፖሊሲዎች አሉ፡፡ እነዚህን ህግጋት መሰረት በማድረግ በሀገሪቱ ውስጥ በየደረጃው በሚገኙ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የማኅበረሰብ ተቋማት አማካኝነት ለሴቶች ጥበቃ እና ከለላ እንዲያገኙ እየተሰራ ያለ ቢሆንም እነኚህን ሕግጋት በወጡበት አግባብ በስራ ላይ ማዋል ቀላል ተግባር ባለመሆኑ አሁንም በርካታ ሴት እህቶቻችን የተለያዩ መብቶቻቸው እየተጣሱ ለችግር ሲጋለጡ ይታያሉ፡፡ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ የመብት ጥሰቶች ዘርፈ-ብዙ ሲሆኑ፤ ከወንዶች እኩል የልማት ተጠቃሚ አለመሆን፣ ለሀይል ጥቃት መጋለጥ፣ ከወንዶች እኩል የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ጉዳዮች የመሳተፍ እድል አለመኖር፣ በሀብት ክፍፍል ወቅት የፍትሐዊ ተጠቃሚነት መጓደል እና ሌሎች መብቶቻቸው ያለመከበር ችግሮችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

እነኝህን ለዘመናት ስር ሰድደው የቆዩ ችግሮች ለመቅረፍ ከፍተኛ ጥረትን እና ትግልን ይጠይቃል፡፡ ይህ ጥረት እና ትግል ደግሞ በተናጥል ሳይሆን በጋራ እና በትብብር ቢደረግ ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆን በመታመኑ የአማራ ሴቶች ማኅበር በአለም-አቀፍና በአህጉር የሕግ ማዕቀፎች እና አገራችን ኢትዮጵያም የተቀበለቻቸውን ሕጐች መሠረት በማድረግ በክልሉና ከክልሉ ውጭ ያሉ የአማራ ሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንዲቻል አስተባብሮ ለመምራት የተደራጀ ያታዊ ማኅበር ነው፡፡
ማኅበሩ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ የተቋቋመ ሲሆን በቆይታው በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ እና በፖለቲካዊ ዘርፎች በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ የሴቶችን መብት በማስከበር ረገድም የተመዘገቡ ለውጦች ከፍተኛ ቢሆኑም ከችግሩ ስፋትና ጥልቀት አኳያ ገና ብዙ ትግል የሚጠይቅ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

በመሆኑም ያገኘናቸው ድሎችን እየጠበቅን የቀሩትን ተግባራት ለማከናወን በሕግና ሥርዓት መመራት ተገቢ በመሆኑ ከዚህ በፊት ማኅበሩ ከምስረታ ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 23 ዓመታት ሲመራበት የነበረውን ህገ ደንብ ማህበረሰባችን በተለይም ሴቶች አሁን ከደረሱበት የአስተሳሰብ ደረጃ እና ከአጠቃላይ ሀገራዊ አሰራሮች እና ህጎች መሻሻል አኳያ ወቅቱን የቃኘ፣ አሁን ካለው የአባሎቻችን ሁለንተናዊ ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ተቋምና አሰራር ከመፍጠር፣ ከጊዜው ጋር የሚራመድ እና ማህበራችንን ወደፊት ሊያስቀድም የሚችል ህገ ደንብ በማስፈለጉ የተሻሻለው ሕገ-ደንብ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

# <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### 1 <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአማራ ሴቶች ማኅበር /አሴማ/ሕገ-ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ሕገ-ደንብ ውስጥ፡-

2.1 **"የአማራ ሴቶች ማኅበር" ማለት በክልሉ የሚኖሩ ከክልል ውጭ የሚገኙ የክልሉ ተወላጅ ሴቶች** ዕድሜያቸው ለመደራጀት የደረሱ በሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ዙሪያ የጋራ ፍላጎትና ዓላማ ባላቸው ሴቶች የተመሠረተ፣ ከማንኛውም ፖለቲካዊ ወገንተኝነት ነፃ የሆነ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ የበጎ አድራጎትና የፆታ ማህበር ነው፤

2.2 **"ጠቅላላ ጉባኤ"** ማለት ከሁሉም የማህበሩ መዋቅሮች በምርጫ የተወከሉ አባሎችን የያዘ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው፤

2.3 **"ምክር ቤት"** ማለት የአማራ ሴቶች ማህበር ምክር ቤት ነው፡፡

### 3. <u>ስያሜ</u>

የማህበሩ መጠሪያ "የአማራ ሴቶች ማኅበር /አሴማ/" ተብሎ ይጠራል፡፡

### 4. <u>መቋቋም</u>

የአማራ ሴቶች ማህበር የተባለ ሀገር በቀል ሲቪክ ማህበር በመሆን ዛሬ ግንቦት ---- ቀን 1990 ዓ.ም በአባላቱ ስምምነት ተመስርቷል፡፡

## 5. <u>ዓላማ፣ ራዕይና ተልእኮ</u>

### 5.1 ዓላማ

የአማራ ሴቶች ማህበር ከዚህ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

5.1.1 በአገራችን ሕገ-መንግሥት እና ሌሎች ሕጎች እንዲሁም በአለም አቀፍ ስምምነቶች ጥበቃ የተደረገላቸው የሴቶች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩላቸው መታገል፤

5.1.2. የማኅበሩ አባላት እና የክልሉ ሴቶች ሁለገብ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ማስቻል ነው፡፡

**5.2 የአማራ ሴቶች ማህበር ራዕይ**

**ራዕይ**

- በ2030 የሴቶችን ሁለንተናዊ መብት የሚያከብር ማህበረሰብ ተፈጥሮ ማየት

**5.3 የአማራ ሴቶች ማህበር ተልዕኮ**

**ተልዕኮ**

- የተጠናከረ እና ሁሉንም የክልሉ ሴቶች አባል የሆኑበት ማህበር በመገንባት፤ የሴቶች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና የመልካም አስተዳደር ችግር ተፈትቶ፤ ሴቶች ከፆታዊ ትንኮሳና ጥቃት ነፃ እንዲሆኑ፣ ማህበረሰቡን በማንቃትና በማደራጀት ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር የስርዓተ ፆታ እኩልነት እንዲረጋገጥ መስራት፡፡

## 6. <u>የማኅበሩ አርማ እና ትርጉም</u>

6.1 ማኅበሩ አርማ የምሁራን እና አርሶ-አደሯን ሴት ውክልና የያዙ ሁለት ሴቶች በክብ መሀል የሚታዩበት፣ ዙሪያው ግማሽ የኢንዱስትሪና ግማሹ የግብርና ውጤት የሆነው የስንዴ ዘለላ የተከበበ ሆኖ በአማርኛና እንግሊዘኛ የማኅበሩን ሙሉ ስያሜ የያዘ ነው፤

6.2 የአርማው ትርጉም፡- ሴቶች ለሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው መከበርና መጠበቅ በተደራጀ አግባብ የሚያደርጉት የጋራ ትግላቸውን እና ተጠቃሚነታቸውን የሚያመላክት ነው፡፡

## 7. <u>የማኅበሩ ዋና ጽህፈት ቤት</u>

7.1 የአማራ ሴቶች ማኅበር ዋና ጽህፈት ቤት መቀመጫ በክልሉ ዋና ከተማ ባህርዳር ይሆናል፤

7.2 በዚህ አንቀጽ 7.1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማኅበሩ በዞን /በብሔረ-ሰብ አስተዳደር/፣ በሬጂዮ ፖሊታን ከተማ አስተዳደር፣ በወረዳ /በከተማ አስተዳደር/ እና በቀበሌ ደረጃ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ክልሎች፣ በፌዴራል ከተሞችና ከአገር ውጭ ጽህፈት ቤቶች ይኖሩታል፡፡

## 8. <u>የማኅበሩ ተግባር እና ኃላፊነት፦</u>

ማኅበሩ ዓላማዎቹን ለማሳካት ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

8.1 ሴቷ መሠረታዊ ትምህርት፣ ስልጠናና የሥራ ዕድል የምታገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

8.2 በአገሯ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ረገድ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራት ያበረታታል፤

8.3 ሴቷን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የተለያዩ የስልጠናና የአቅም ግንባታ መርሃ-ግብሮችንና ፕሮጀክቶችን ይዘረጋል፣ ያስፈፅማል፤

8.4 ዓላማዎቹን ከሚደግፉ መሰል የልማትና የግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ጋር ግንኙነቶችን ያደርጋል፣ ተባብሮ ይሠራል፤

8.5 የማኅበሩን አባላት በተዘዋዋሪ ብድር አገልግሎት፣ በቀጥታ የገንዘብ ድጋፍ እና በመሳሰሉት መንገዶች በማገዝ ከድህነት እንዲወጡ ጥረት ያደርጋል፤

8.6 መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት እና ህዝቡን በማስተባበር ወይም በህዝባዊ መዋጮ ማኅበሩን በገቢ ያጠናክራል፤

8.7 ለማኅበሩ አባላት የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል፤

8.8 ማኅበሩ ከፖለቲካ ድርጅቶች ነፃነቱን ጠብቆ የማኅበሩ አባላትን ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የሚፈታ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋል ጥቅሙን የሚፃረሩትን ደግሞ በተደራጀ እና በሰላማዊ መንገድ እንዲስተካከሉ ይታገላል፤

8.9 ውሎችን ይዋዋላል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

8.10 ፆታን መሠረት ተደርጎ የሚፈፀሙ ጥቃቶችና ጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከልና ምላሽ መስጠት

8.11 የሴቶችን የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲፈቱ መስራት

8.12 ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚረዱ እና ከዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

## ክፍል ሁለት

## መርሆዎች፣እሴቶች፣ አባልነት እና የገቢ ምንጭ

### 9. መርሆዎች

የአማራ ሴቶች ማኅበር መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፦

9.1 በጎ ፈቃደኝነት፤

9.2 አርአያነት፤

9.3 ፍትሓዊ ተጠቃሚነት፤

9.4 የሕግ የበላይነት፤

9.5 ዴሞክራሲያዊነት፤

9.6 ህዝባዊነት፤

9.7 አጋርነት፤

### 10. እሴቶች

የማኅበሩ እሴቶች ከዚህ የሚከተሉት ይሆናሉ፦

10.1 ለአባላት የላቀ ተሳትፎና ተጠቃሚነት መትጋት፤

10.2 ግልጽነት፤

10.3 ተጠያቂነት፤

10.4 አሳታፊነት እና ውጤታማነት፤

10.5 ከመንግሥት መርሆዎች ጋር የተጣጣመ አሠራርን መከተል።

## 11. ለአባልነት የሚያበቁ ሁኔታዎች

የሚከተሉትን መመዘኛዎች የምታሟላ ሴት የአማራ ሴቶች ማኅበር ሙሉ አባል መሆን ትችላለች፡-

11.1 እድሜዋ18 እና በላይ የሆነች፤

11.2 የማኅበሩ አባል ለመሆን ፍላጐት ያላት እና ፍላጐትዋን ያሳወቀች፤

11.3 የማኅበሩን ኘሮግራምና ሕገ-ደንብ የተቀበለች፤

11.4 የማኅበሩ ዓላማ ግቡን እንዲመታ በየደረጃው ባሉ የሥራ እርከኖች ገብታ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነች፤

11.5 ከክልሉ ውጭም ሆነ በውጭ አገራት የሚኖሩ የክልሉ ተወላጅ የሆኑ ፍላጎት ያላቸው ሴቶች በአባልነት መደራጀት ይችላሉ፤

11.6 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11.5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማኅበሩን ለማጠናከር ፍላጎቱ ያላቸው ወንዶች እና ከክልሉ ተወላጆች ውጭ ያሉ ሴቶች ተባባሪ አባል መሆን ይችላሉ፤

11.7 የማኅበሩን ራዕይና ተልዕኮ ተቀብለው የሚደግፉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተባባሪ አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡

## 12. የማኅበር አባልነት መብት

የማኅበሩ አባል የሆነች ሴት የሚከተሉት መብቶች ይኖሯታል፦

12.1 በሁሉም የማኅበሩ ጉባኤዎች እና የተለያዩ አስተዳደር እርከኖች ትወክለኛለች የምትላትን ሴት የመምረጥ፣ የመመረጥ እና ማኅበሩ በሚያዘጋጀው ልዩ ልዩ መድረኮች የመሳተፍ፤

12.2 ሃሳቧንና አስተያየቷን በነጻ የመግለጽና በየደረጃው በሚገኙ አመራሮች የሚታዩ ጉድለቶችን በማቅረብ የመገምገም፤

12.3 የማኅበሩን የሥራ እንቅስቃሴ መረጃ የመጠየቅና የማግኘት፤

12.4 ማኅበሩ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት ከሚተገብራቸው ኘሮግራሞች ተጠቃሚ የመሆን፤

12.5 መብቷንና ነጻነቷን የሚጋፉ ተግባራት ሲፈፀሙ የማኅበሩ አቅም በፈቀደው መጠን ድጋፍ የማግኘት፤

12.6 የማኅበሩን የአባልነት መታወቂያ የማግኘት፤

12.7 በፈለገች ጊዜ ከማኀበሩ የመውጣት፤መብት አላት።

## 13. የማኀበር አባልነት ግዴታ

የማኀበሩ አባል የሆነች ሴት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩባታል፡-

13.1 ለማኀበሩ ኘሮግራምና ሕግ ተግባራዊነት ተገዥ መሆን፤

13.2 በማኀበሩ ጉባኤ የመገኘትና የመሳተፍ፤

13.3 ጉባኤው የወሰነውንና የሚወስነውን የአባልነት ክፍያ ወይም መዋጮ የመክፈል፤

13.4 ማኀበሩ በሚያከናውናቸው የልማት እንቅስቃሴዎች የመሳተፍ፤

13.5 የማኀበሩን ሕልውና የሚቃረን ተግባር አለመፈፀም እንዳይፈፀምም በጽናት የመታገል፤

13.6 የማኀበሩ ኘሮግራም በሌሎች ዘንድ ይበልጥ እንዲታወቅ የመጣርና አባላትን የማፍራት፤

13.7 በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ከማኀበሩ የተሰናበተች እንደሆነ ከማህበሩ የተሰጣትን የአባልነት መታወቂያ ካርድ የመመለስ፤

13.8 በማንኛውም ሁኔታ ላጠፋችው ጥፋት ተጠያቂ የመሆን ግዴታ ይኖርባታል።

## 14. አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

ማንኛዋም የማኀበሩ አባል የሆነች ሴት አባልነቷ ሊቋረጥ የሚችለው ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ይሆናል፡-

14.1 ከአባልነት ለመልቀቅ በፍላጐቷ ጥያቄ ስታቀርብ፤

14.2 የማኀበሩን ዓላማና ኘሮግራም የሚቃረን ተግባር ፈጽማ ስትገኝና በማኀበሩ ሕግ መሠረት በማኀበሩ አመራሮች እንድትሰናበት ሲወሰን፤

14.3 የማኀበር የአባልነት ክፍያ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ያለ በቂ ምክንያት ያልከፈለች እንደሆነ፤

14.4 በራሷ ምክንያት የማኀበሩን ዓላማ የሚቃረን ሥራ በመፈፀሟ ከአባልነት የተሰናበተች የማህበሩ አባል ከዚህ በፊት የከፈለችውን ገንዘብም ሆነ ሌላ ያደረገችው ድጋፍ ካለ እንዲመለስላት የመጠየቅ መብት አይኖራትም፤

14.5 በሞት የተለየች ሴት ከአባልነት እንደተሰናበተች ይቆጠራል፡

## 15. የውሳኔ አሰጣጥ

15.1 የማኀበሩ አባል የሆነች ሴት በማንኛውም ጉዳይ ላይ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት በነጻ የመወያየትና የመከራከር መብቷ ያለገደብ የተጠበቀ ነው፤

15.2 ለማኀበሩ አባላት ለውይይት የቀረበ የመወያያ አጀንዳ በቂ ውይይት ከተካሄደበት በኋላ

ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፤

15.3 ውሳኔዎች በስብሰባው ላይ በተገኙ የማኅበሩ አባላት አብላጫ ድምጽ ይተላለፋሉ፤

15.4 የተሰብሳቢዎች ድምጽ እኩል ከመጣ ሰብሳቢዋ ያለችበት ወገን አሸናፊ ይሆናል፤

15.5 የዚህ ሕገ-ደንብ 14.3 እና 14.4 ድንጋጌ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ በድምጽ የተለዩ የማኅበሩ አባላት ልዩነታቸውን ይዘው የመከራከር መብታቸው የተጠበቀ ነው፤

15.6 ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ቅሬታ ያላት የማኅበር አባል ለማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔው እንደገና እንዲታይ መጠየቅ ትችላለች።

## 16. የማኅበሩ የገቢ ምንጭ

ማኅበሩ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፡-

16.1 ከአባላት የሚሰበሰብ መዋጮ፤

16.2 ከግለሰቦች፣ ከመንግሥትና ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚገኝ የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ ወይም እርዳታ፤

16.3 ማኅበሩ ከሚያቋቁማቸው የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች፤ይሆናል።

# ክፍል ሦስት

## አወቃቀር

## 17. የማኅበሩ አወቃቀር

17.1 የአማራ ሴቶች ማኅበር በክልሉ ውስጥ በክልል፣ በዞን /በብሔረ-ሰብ አስተዳደር/፣ በሪጂዮ ፖሊታን ከተማ አስተዳደር፣ በወረዳ /በከተማ አስተዳደር/ እና በቀበሌ ደረጃ የሚዋቀር ይሆናል፤

17.2 በዚህ አንቀጽ 17.1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማኅበሩ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች፣ የፌደራል ከተማ አስተዳደሮችና የውጭ አገር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ሊያቋቁም ይችላል።

## 18. የማኅበሩ አጠቃላይ አደረጃጀት

የአማራ ክልል ሴቶች ማኅበር አደረጃጀት/መዋቅር/ እንደሚከተለው ይሆናል፦

18.1 ጠቅላላጉባኤ፤

18.2 ምክርቤት፤

18.3 ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን፤

18.4 የሥራ አመራር ቦርድ፤

18.5 የክልል እና ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች፤

18.6 የሥራ አመራር ኮሚቴ፤

18.7 ልዩ ልዩ የስራ ክፍሎች፡፡

## 19. ጠቅላላ ጉባኤ

ጠቅላላ ጉባኤው ከሁሉም የማኅበሩ አደረጃጀቶች በምርጫ የተወከሉ አባሎችን የያዘ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ፦

19.1 የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በየሶስት አመቱ አንድ ጊዜ ይካሄዳል፤

19.2 ጠቅላላ ጉባኤ እስኪደርስ ሊቆዩ የማይችሉ ጉዳዮች አሉ ተብሎ ጥያቄ ሲቀርብና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በምክር ቤቱ ውሣኔ ወይም ከማኅበሩ አባላት አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት ፊርማ በማሰባሰብ ከጠየቁ ወይም አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት የኦዲት ኮሚሽን አባላት ጥያቄ ካቀረቡ አስቸኳይ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል፤

19.3 አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው በተያዘለት ጊዜ ሊካሄድ የማይችል ከሆነየሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውአባላት ውይይት አድርገውበት ለተጨማሪ ስድስት ወራት ሊያራዝሙት ይችላሉ፤

19.4 ከዚህ በላይ ተጨማሪ ስድስት ወር ሊራዘም የሚችለው ግን ከማኅበሩ ምክር ቤት አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሲደግፉት ብቻ ይሆናል፤

19.5 ከዚህ በላይ በተገለፀው መሠረት የሚጠራ አስቸኳይ ጉባኤ እንደ መደበኛ ጉባኤ ተመሣሣይ ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፤

19.6 የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴው ባስመረጣቸው ኘሬዚዲየሞች የሚመራ ሲሆን አስቸኳይ ጉባኤ ሲጠራ ግን በቦርድ ሰብሳቢዋ የሚመራ ይሆናል፡፡

## 20. የጠቅላላ ጉባኤው ሥልጣን እና ተግባር

የአማራ ሴቶች ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ በዚህ ሕገ-ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

20.1 ማኅበሩ የሚመራባቸውን ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ያጸድቃል፤

20.2 በአዘጋጅ ኮሚቴው እና በሌሎች የጉባኤው ተሳታፊዎች በሚቀርቡ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ያስተላልፋል፤

20.3 የአለፉትን ሶስት አመታት የሥራ ሪፖርት አዳምጦ ውይይት በማድረግ ያፀድቃል፣ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ውሳኔዎች ያስተላልፋል፤

20.4 እስከ ቀጣዩ ጉባኤ ድረስ የሚሰሩ ሥራዎችን እቅድ ያጸድቃል፤

20.5 የማኅበሩን የቦርድ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ ወይም የጉባኤ ተሳታፊ አዘጋጅ ኮሚቴ ውክልና ከተሰጣቸው ጉባኤተኞች ይመርጣል፤

20.6 የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብና ኘሮግራም ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፤

20.7 የኦዲት ሪፖርት አዳምጦ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፤

20.8 የማህበሩን የምክር ቤት፣ የስራ አመራር ቦርድ እና የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላትን ይመርጣል፣ ያግዳል፣ ያሰናብታል፤

20.9 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማኅበሩ እንዲፈርስ ይወስናል።

## 21. ምልዓተ-ጉባኤና የድምጽ አሰጣጥ ሂደት

21.1 ምልዐተ-ጉባኤው ከሁሉም በክልሉ ከሚገኙ እና ከክልሉ ውጭ ካሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚወከሉ ጉባኤተኞች ይኖሩታል።

21.2 ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የጠቅላላ ጉባኤው አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ- ጉባኤ ይሆናል፤

21.3 ውሳኔዎችም በስብሰባው ላይ በተገኙ 50+1 አባላት ድምጽ ይተላለፋሉ፤

21.4 የጉባኤተኞች ድምፅ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ እንደገና ውይይት ተደርጎበት ተከራካሪዎች እንዲሳሳቡ ይደረጋል፣ ይህ ሆኖ መሳሳብ ካልተቻለ በጉባኤዉ ሰብሳቢ የተደገፈው ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፤

21.5 በጉባኤው የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላት በሙሉ ድምጽ የሚሳተፉ ሲሆን ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ያለድምጽ ተሳታፊ ይሆናሉ።

## 22. ስለ ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ

22.1 የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ የሚቋቋመው በማኅበሩ ሥራ ስራ አመራር ቦርድ አማካኝነት ነው፤

22.2 የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶችይኖሩታል፡-

ሀ) ሎጂስቲክስ እና ሌሎች ለጉባኤ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን የማዘጋጀት፤

ለ) የአዘጋጅ ኮሚቴውን ሪፖርት ለጉባኤ አቅርቦ በማስፀደቅ አምስት አባሎች ያሉበት አስመራጭ ኘሬዚድየም አስመርጦ ሥራውን ያጠናቅቃል።

## 23. የምክር ቤቱ አመራረጥ እና አሠራር

23.1 የምክር ቤቱ አባላት ከጉባኤተኞች ወይም ከውጪ በግልጽ ወይም በሚስጥር በሚሰጥ ድምጽ በምልዐተ-ጉባኤው የሚመረጡ 65 /ስድሳ አምስት/ አባላት ይሆናሉ፤

23.2 የምክር ቤቱ አባላት ስብሰባ የቦርድ ሰብሳቢዋ የሚመራ ሆኖ በ6ወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል፤

23.3 የዚህ አንቀጽ 23.2 ድንጋጌ ቢኖርም አስቸኳይ ስብሰባ በቦርድ ሰብሳቢዋ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት 1/3ኛው ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል፤

23.4 ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤

23.5 ውሣኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ላይ ከተገኙት የምክር ቤት አባላት ከግማሽ በላይ /50+1/ የድምጽ ድጋፍ ይሆናል፤

23.6 ውሳኔው በእኩል ድምጽ የተለያየ እንደሆነ ሰብሳቢዋ ያለችበት ወገን አሸናፊ ይሆናል፡፡

## 24. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

የማኅበሩ ምክር ቤት እስከ ቀጣይ ጉባኤ ጊዜ ድረስ የማኅበሩ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራት ይኖሩታል፡-

24.1 አጠቃላይ የማኅበሩን እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፤

24.2 የጉባኤው ውሣኔዎችና ዓላማዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ክትትል ያደርጋል፤

24.3 ሴቶች በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያነሳሳል፣ ይሠራል፤

24.4 የማኅበሩን ገንዘብና ንብረት ይቆጣጠራል፣ ዓመታዊ እቅድና በጀት ደልድሎ ያፀድቃል፤

24.5 የምክር ቤቱን ውሳኔዎችና የውይይት ሂደት በቃለ-ጉባዔ ተይዞ በቀጣዩ መደበኛ ስብሰባ እንዲጸድቅ ያደርጋል፤

24.6 በአዲስ የተመረጡና የሚተኩ የሥራ አስፈጻሚኮሚቴ አባላትን ሹመት ያፀድቃል፤

24.7 የተለያዩ ጥፋቶችን የፈጸሙና ሥራቸውን በአግባቡ ያላከናወኑ የምክር ቤቱን እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ከሥራቸው ያግዳል፣ አጣርቶም ለጠቅላላ ጉባኤው እንዲሰናበቱ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣በሕግ የሚያስጠይቁ ጉዳዮች ሲኖሩ እንዲጠየቁ ያደርጋል፤

24.8 የማኅበሩን የፋይናንስ፣ የሰው ሃይል አስተዳደር፣ ተቋማዊ መዋቅሩንና የተለያዩ መመሪያዎችን ያፀድቃል፤

24.9 የማኅበሩን የየበጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት ይሰማል፣ መርምሮ ያፀድቃል፤

24.10 የማኅበሩን ዓመታዊ በጀት መርምሮ ያፀድቃል፤

24.11 የማኅበሩ አሠራሮችን ይከታተላል፣ ችግር አለ ብሎ ሲያምን ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ ያደርጋል፡፡

## 25. በየደረጃው ያሉ ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽኖች

25.1 በየደረጃው በሚኖረው ጉባኤ የተመረጡና ተጠሪነታቸውም በክልል ደረጃ ለስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢዋ የሆኑ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽኖች በክልል እና በዞን /በብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር፣ በክፍለ-ከተማ እና በቀበሌ ደረጃ ይቋቋማሉ፣

25.2 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላት ብዛት በክልል አምስት፣ በዞን /በብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም በሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር፣ በክፍለ-ከተማ እና በቀበሌ ሶስት ሶስት ይሆናሉ፤

## 26. የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር

26.1 በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የአባላት መብት እንዲከበር ይንቀሳቀሳል፤

26.2 የማኅበሩን ደንብና አሠራር መጠበቁን ክትትል ያደርጋል፤

26.3 ከአባልነት የተባረረች የማኅበሩ አባል ያለአግባብ ተባርሬያለሁ የሚል ቅሬታ ያቀረበች እንደሆነ አስፈላጊ ማጣራት በማድረግ ጉዳዩ በስምምነት እልባት እንዲያገኝ ይጥራል፣ በስምምነት ያላለቀ እንደሆነ አስተያየቱን ለጠቅላላ ጉባኤው በማቅረብ በጉባኤው የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፤

26.4 የማህበሩን የሒሳብ ሰነዶች፣ መዛግብትንና ንብረትን ይመረምራል፣ ያጣራል፣ የተገኘውን ውጤት ለጉባኤው ያቀርባል፤

26.5 ተግባርና ኃላፊነቱን ለመፈፀም በሚያደርገው የማጣራትና የምርመራ ሒደት በየደረጃው ካሉት የስራ አመራር ቦርድ አባላት አስፈላጊውን መረጃ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፣ የስራ አመራር ቦርድ አባላትም ይህንኑ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፤

26.6 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን በጉባኤ ፀድቆ በሥራ ላይ የሚውል የራሱ አደረጃጀት መመሪያ ይኖረዋል፤

26.7 አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነና 1/3ኛ የሚሆኑትን የአባላት የድጋፍ ፊርማ ካገኘ አስቸኳይ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል፡፡

# ክፍል አራት

## በየደረጃው ስለሚኖረው የማህበሩ አደረጃጀት፣ ተግባር እና ኃላፊነት

## 27. የክልሉ ሥራ አመራር ቦርድ

27.1 የክልል ሥራ አመራር ቦርድ ኮሚቴ እስከ 13 አባላት ያሉት ሆኖ የሚዋቀር ሲሆን፤ ተጠሪነቱም ለምክር ቤቱ ይሆናል፤

27.2 ኮሚቴው ከምክር ቤት አባላት መካከል በግልጽ /በሚስጥር/ በሚሰጥ ድምጽ ይመረጣል፤

27.3 ከየዞኑ /የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም ከሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች የተመረጡ ሥራ አመራር ቦርድ አባላት የዞኑ /የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩ የቦርድ ሰብሳቢ ይሆናሉ፤

27.4 የማኅበሩ ሥራ አመራር ቦርድ አባላትሆነው የሚመረጡ ተመራጮችለሴቶች ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ የኢኮኖሚ ፣ የማህበራዊ፣ መልካም አስተዳደርና ውሳኔ ሰጭ ከሆኑ ተቋማት የሚገኙ ጠንካራ ሴቶች ፣ በሴትነት ጾታቸው ከተደራጁ ሲቪክ ማህበራት ፣ተጽኖ ፈጣሪ ከሆኑ ሴቶች እንዲሁም በጉባዔ ከተመረጡ የምክር ቤት አባላት እና ውጭ ከ9 እስከ 13 አባላት ያሉት ሆኖ ይዋቀራል

27.5 ሥራ ሥራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ፣ ም/ሰብሳቢ፣ እና አባላት ይኖሩታል

27.6 አመራር ቦርድ በሰብሳቢዋ ይመራል፣

27.7 የሥራ አመራር ቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ይደረጋል፣

27.8 አስቸኳይ ስብሰባ በቦርድ ሰብሳቢዋ ወይም ከሥራ አመራር ቦርድ አባላት 1/3ኛው ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል፣

27.9 የሥራ አመራር ቦርድምልዓተ-ጉባኤ ከአባላቱ 50%+1 የተገኙበት ይሆናል፣

27.10 ሥራ አመራር ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ከሁለት ጊዜ ተከታታይ የምርጫ ዘመን ሊበልጥ አይችልም፡፡

## 28. የክልል ሥራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

28.1 የማኅበሩን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ የጉባኤውንና የምክር ቤቱን ውሳኔዎችና ሕገ-ደንቡን መሠረት በማድረግ የማኅበሩን ረቂቅ መመሪያዎች ያወጣል፣ተግባራዊ መሆናቸውንም ይከታተላል፣

28.2 የማኅበሩን ውሣኔዎችና አቅጣጫዎች ለማኅበሩ አባላትና ለመላው ሴቶች ተደራሽ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፣

28.3 ለምክር ቤቱ መወያያ አጀንዳ ያዘጋጃል፣

28.4 ለምክር ቤቱ የሥራ እቅድና ሪፖርት አቅርቦ ያስጸድቃል፣

28.5 በጉባኤውና በምክር ቤቱ የሚወጡና የሚጸድቁ እቅዶች፣ አቅጣጫዎች፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች መከበራቸውን እና በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ አመራር ይሰጣል፣

28.6 የሴቶች የመልካም አስተዳደርና ውሳኔ ሰጭነት ተሳትፎ እንዲያድግ ይሠራል፣

28.7 በፀደቀው ዕቅድ መሠረት የበጀትና የሰው ኃይል ስምሪት ያደርጋል፣

28.8 በየደረጃው የሚገኙ የማኅበሩን መዋቅሮች የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

28.9 ለማኅበሩ ጽህፈት ቤት የሥራ መመሪያ ይሰጣል፣

28.10 የሥራ አመራር ቦርድ አባላትም ሆነ ሌሎች አባሎችን በተለያየ የማኅበሩ ሥራ ላይ ይመድባል፣

28.11 በዞን /በብሔረ-ሰብ አስተዳደር/፣ በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር፣ በክፍለ-ከተማ እና በቀበሌ ያሉ ልዩ ልዩ ገቢ ማስገኛ ተግባራትን ይመራል፣ በአስተዳደር ጉዳዮች ላይ መመሪያ ያስተላልፋል፤

28.12 የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ይሰይማል፣ ዝርዝር የሥራ መመሪያ ያወጣል፤

28.13 የሥራ አመራር ቦርድከተግባርና ኃላፊነቱ በከፊል ለማጎበሩ የጽ/ቤት አመራሮች ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

28.14 በየደረጃው ያሉ የአመራሮች ሥራቸዉን በተገቢዉ እየመሩ መሆኑን ይከታተላል፣በእነሱ የሚቀርቡ አጀንዳዎችን መርምሮ ያፀድቃል፤

28.15 ሌሎች የጠቅላላ ጉባኤውና የምክር ቤቱሥልጣን ያልሆኑ ለማህበሩ ሥራ መቃናት ትርጉም ያላቸዉን ተግባራት ሁሉ በበላይነት ይመራል::

## 29. የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢዋ ተግባርና ኃላፊነት

29.1 ሊቀመንበሯ ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት በጉባኤተኛ ተመርጣ ተጠሪነቷ ለጠቅላላ ጉባኤውና ለምክር ቤቱ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል

29.2 የጠቅላላ ጉባኤውን አስቸኳይ ስብሰባዎች ትመራለች

29.3 የምክር ቤቱን እና የቦርዱን ስስበባዎችን በሰብሳቢነት ትመራለች

29.4 የጠቅላላ ጉባኤውን ተግባር ታስተባብራለች ውሳኔነውን ታስፈጽማለች

29.5 የማህበሩን ተግባራት ትገመግማለች አቅጣጫ ታስቀምጣለች

## 30. የስራ አመራ ቦርድ ም/ሰብሳቢዋ ተግባርና ኃላፊነት

ምክትል ሰብሳቢዋ ከጠቅላላ ጉባኤው መካከል በጉባኤተኞች ተመርጣ ተጠሪነቷ ሰብሳቢዋ፤ ለም/ቤቱና ለቦርዱ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል ፡፡

30.1 የቦርድ ሰብሳቢዋ በማትኖርበት ወይም ስራዋን ለማከናወን በማትችልበት ጊዜ ተክታ ትሰራለች

30.2 የሚሰጡ ውሣኔዎችንና አቅጣጫናዎችን ከሰብሳቢዋ ጋር በመመካከር ትሰራለች

30.3 ከሰብሳቢዋ ቀጥላ ቦርዱን የሥራ እቅድ ታወርዳለች አፈጻጸሙን ትከታተላለች

30.4 በስራ አመራር ቦርዱ አባላትና በሰብሳቢዋ የሚሰጣትን ተግባር ታከናውናለች

## 31. የክልል ጽህፈት ቤት

የአማራ ሴቶች ማህበር ክልል ጽ/ቤት በዚህ ህገ ደንብ አንቀጽ 8 ስር ለማህበሩ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ከጽ/ቤቱ ስራ ጋር በቋሚነት የሚመሩ የማህበሩ ዋና ዳይሬክተር፤ ሁለት

ምክትል ዳይሮክተሮች እንዲሁም ሌሎች ለማህበሩ አስፈላጊ የሆኑየስራ ዘርፎችን የሚመሩ አስተባባሪዎችና ባለሙያዎች ይኖሩታል፡፡

## 32. የማህበሩ ዋና ዳይሬክተር ተግባርና ኃላፊነት

32.1 በምደባ ወይም በቅጥር በሜሪት የምትመደብ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሯታል፡፡

32.2 የማህበሩን ጽ/ቤት በበለይነት ትመራለች፣ ታስተባበራለች

32.3 ማህበሩን በመወከል ከ3ኛ ወገን ጋር ግንኙነት ታደርጋለች ውሎችንና ስምምነተትን ትፈራረማለች

32.4 በተቋሙ ውስጥ የሚፈፀሙ ኘሮጀክቶችን ታስተባብራለች ትከታተላለች፣

32.5 የኢኮኖሚ ዘርፉን፤ የማህበራዊ ፤ የመልካም አስተዳደርና ዉሳኔ ሰጭነት ዘርፉን በበላይነት ታስተባብራለች

32.6 ለማህበሩ የቦርድ አባላት የሥራ ሪፖርት ታቀርባለች

32.7 በተዋረድ ያሉትን የማህበሩን መዋቅሮች በበላይነት ትመራለች ታስተባብራለች ትከታተላለች

32.8 የሥራ አመራር ኮሚቴ በሰብሳቢነት ትመራለች

32.9 በቦርድ አባላት የሚሰጣትን ሌሎች ተግባራት ታከናውናለች

## 33. የማህበሩ ምክትል ዳይሬክተሮች ተግባርና ኃላፊነት

በቅጥር ወይም በምደባ በሜሪት የሚመደቡ ሆና የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሯታል

33.1 አንደኛዋ የኢኮኖሚ ዘርፉን አንደኛዋ ደግሞ የማህበራዊ ፤የመልካም አስተዳደርና ዉሳኔ ሰጭነት ዘርፉን ትመራለች

33.2 የማህበሩ ምክትል ስራ አስፈጻሚዎች ከማህበሩ ዋና ስራ አስፈጻሚ ቀጥለው ያስተባብራሉ ይመራሉ ይከታተላሉ

33.3 የማህበሩን ጽ/ቤት እቅድ ለተዋረድ የማህበሩ መዋቅር የየዘርፋቸውን ያወርዳሉ አፈጻጸሙን ይከታተላሉ ይደግፋሉ

33.4 የቦርድ አባላት ስበሰባ ያለድምጽ ይሳተፋሉ አንደኛዋ ቃለጉባዔ ትይዛለች በተቋሙና በተዋረድ ያሉ የማህበሩን ፈጻሚዎች ይከታተላሉ ያበቃሉ ችግር ሲኖር የእርምት እርምጃ ይወስዳሉ

33.5 በተቋሙ ውስጥ ያሉ ንበረቶችንና ሌሎች የማህበሩ ሀብቶች ለብክነት እንዳይዳረጉ ተገቢውን መመሪያ ይሰጣሉ ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮችን ለስራ አስፈጻሚዋ ያቀርባሉ፡፡

## 34. የማህበራዊ ፤መልካም አስተዳደርና ውሳኔ ሰጭነት ዘርፍ የምትመራው ምክትል ዳይሬክተር

34.1 የአባላት የማህበራዊ ዘርፍ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ትከታተላለች

34.2 አባላት በትምህርት ዘርፍ የትምህርት ተሳትፎና ጥራት በማሣደግ ደረጃ አበርክቷቸውና ተጠቃሚነታቸውን ትከታተላለች ትገመግማለች

34.3 የአባላት በጤናው ዘርፍ ያላቸውን አበርክቶና ተጠቃሚነት በተመለከተ ትከታተላለች ትገመግማለች

34.4 በአባላት እየገጠሟቸው ያሉ እና ሊገጥሟቸው የሚችሉ የመልካም አስተዳደር እጦት ችግሮችን ትከታተላለች ትገመግማለች

34.5 በሴቶች ላይ የሚከሰቱ የሰባዊ መብት ጥሰቶች፣ የፆታዊ ጥቃቶችና የልጅነት ጋብቻን በተመለከተ ትከታተላለች ትገመግማለች

34.6 የሴቶችን የፍትህ እጦት ከሚመለከታቸው አካል ጋር እስከመጨረሻው እንዲፈታ ትሰራለች በዘርፉ ለጽ/ቤቱ ግብዓት ሊሆን የሚችል መረጃና ሪፖርት ታቀርባለች

34.7 አባላት በየዘርፉ የውሳኔ ሰጭነት አቅማቸው እየጐለበተ እንዲሄድ ይሰራል ይከታተላል

34.8 የሴቶች የአመራር ተሳትፎ ተገቢውን ውክልናና የመምራት እድል እንዲያገኙ ይሰራል በየጊዜው በሚካሄዱ ሀገራዊ፣ ክልላዊ፣ የወረዳና የቀበሌ ምርጫዎች ሴቶች 50% እና በላይ የምክር ቤትአባልነት ውክልና እንዲገኙ ይሰራል

34.9 ለዋና ሥራ አስፈጻሚዋ የተደራጀ መረጃና ሪፖርት ታቀርባለች

## 35. የኢኮኖሚ ዘርፍ የምትመራው ምክትል ዳይሬክተር

35.1 የአባላትን በገጠርና በከተማ የኢኮኖሚ አቅም የማሣደግ ተግባርን ትከታተላለች ትደግፋለች ትገመግማለች

35.2 በገቢ ማስገኛ ተግባራት የተሰማሩ አባላትን ውጤታማነትና ተደራሽነት ትከታተላለች ትገመግማለች

35.3 የአባላት የቁጠባ ባህል እንዲጐለብት ይደግፋል ትከታተላለች ትገመግማለች

35.4 የማህበሩ ልዩ ልዩ ሀብት ልየታ እንዲደረግ ህጋዊነትና የሚገኘው ገቢ ለአባላት መዋሉን ትከታተላለች ትገመግማለች አቅጣጫ ታስቀምጣለች

35.5 የአባላትን በአበርክቷቸው ልክ ተጠቃሚ ስለመሆናቸው ትከታተላለች

35.6 ለዋና ሥራ አስፈጻሚዋ የተደራጀ መረጃና ሪፖርት ታቀርባለች

## 36. የማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ

የማህበሩ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል ዳይሬክተር፣ እቅድና ፕሮግራም፣ አስተዳደርና ፋይናንስ ክፍል ሃላፊ ህዝብ ግንኙነትና ሌሎች የስራ ሃላፊዎች በመሆን ከጽ/ቤቱ የጋራ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዩች አይቶ ለመወሰን የሚያስችል ኮሚቴ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

## 37. ስለዞን /ብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት አመራረጥ እና አሠራር

37.1 የምክር ቤቱ አባላት በዞኑ /ብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም ሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩ እና በስራቸው ከሚገኙ ወረዳዎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ተመርጠው የሚወከሉ አባላት ይሆናሉ፤

37.2 የምክር ቤቱ አባላት ስብሰባ በ6 ወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል፤

37.3 አስቸኳይ ስብሰባ በቦርድ ሰብሳቢዋ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት 1/3ኛው ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል፤

37.4 ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የምክር ቤት አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፤

37.5 ውሳኔዎችም በስብሰባው ላይ በተገኙ 50+1 የምክር ቤቱ አባላት ድምጽ የሚተላለፉ ሲሆን፣ የተሰብሳቢዎችድምፅእኩልበእኩልበሚሆንበትጊዜ በምክር ቤቱ ሰብሳቢ የተደገፈው ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፤

37.6 ምክር ቤቱ አንድን ጉዳይ ባብላጫ ድምጽ በሚወስንበት ጊዜ ሁሉ የአነስተኛው ድምጽ አስተያየት በስብሰባው ቃለ-ጉባዔ መመዝገብ ይኖርበታል፤

37.7 የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የራሱን ዝርዝር ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርአት ማስፈጸሚያ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 38. የዞን ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነቶች

38.1 የዞን /የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩን/ ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩን የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ይመርጣል፣ ያፀድቃል፣ ይሽራል፤

38.2 እንደአግባቡ የዞኑን /የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩን/ ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩን ሴቶች ማኅበር እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፤

38.3 የጉባኤው ውሣኔዎችና ዓላማዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ክትትል ያደርጋል፤

38.4 ሴቶች በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ተሳታፊ እንዲሆኑ ያነሳሳል፤

38.5 የማኅበሩን ገንዘብና ንብረት ይቆጣጠራል፣ ከክልል በቀመር የሚላክለትን በጀትና እቅድ ደልድሎ ያፀድቃል፤

38.6 የምክር ቤቱን ውሳኔዎችና የውይይት ሂደቶች በቃለ-ጉባኤ ተይዘው በቀጣዩ መደበኛ ስብሰባ እንዲጸድቁ ያደርጋል፤

38.7 የተለያዩ ጥፋቶችን የፈጸሙና ሥራቸውን በአግባቡ ያላከናወኑ የምክር ቤቱ እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ከሥራቸው ያሰናብታል፤

38.8 የማኅበሩ የሂሳብ አሠራር በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፤

38.9 እንደአግባቡ በዞኑ /የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም በሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩ የሚካሄዱ የገቢ ማስገኛ ተግባራትን እየገመገመ ይመራል።

## 39. የዞን /የብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም ሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር ሥራ አመራር ቦርድ

39.1 የማኅበሩ ሥራ አመራር ቦርድ አባላት ሆነው የሚመረጡ ተመራጮች፤ለሴቶች ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ የኢኮኖሚ፤ የማህበራዊ፤ መልካም አስተዳደርና ውሳኔ ሰጭ ከሆኑ ተቋማት የሚገኙ ጠንካራ ሴቶች፤ በሴትነት ጾታቸው ከተደራጁ ሲቪክ ማህበራት፤ተጽኖ ፈጣሪ ከሆኑ ሴቶች እንዲሁም በጉባዔ ከተመረጡ የምክር ቤት አባላት እናእንደሁኔታው በአስቸጋሪ ጊዜ ከምክር ቤትአባላት ውጭ በዞኑ ምክር ቤት አባላት የሚመረጡ ብዛታቸው 7 አባላትን የያዘ የሥራ አመራር ቦርድ ተጠሪነቱ ለክልል ሥራ አመራር ቦርድ ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

39.2 የማኅበሩን ሕገ-ደንብ ጠንቅቃ በማወቅ የዞን የብሔረ-ሰብ አስተዳደሮችን/ ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሮችን፣ የወረዳዎችን፣ የከተማ አስተዳደሮችንና የክፍለ-ከተሞችንሥራ በኃላፊነት ይመራል፣ይቆጣጠራል፣

39.3 ስለማኅበሩ የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተከታትሎ በመፈጸም በወቅቱ ሪፖርት ያደርጋል፣

39.4 የዞኑን የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩን ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩን የሴቶች ማኅበር ሥራ በበላይነት ይመራል፣

39.5 በተዋረድ የሚገኙ ማኅበራትን መዋቅሮች የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

39.6 ከክልል የሚወርዱ እቅዶች፣ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን ያስፈጽማል፣

39.7 ለዞኑ/የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩሥራ ማስኬጃ የሚመደበውን በጀትና ለወረዳዎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ወይም ክፍለ-ከተሞች

የሚላከውን በጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

39.8 የክልሉን እቅድ መነሻ በማድረግ የዞኑን /የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩን/ ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩን እቅድ በማቀድ ለወረዳዎች፣ ለከተማ አስተዳደሮች፣ ለክፍለ-ከተሞችእና ለቀበሌዎች ያወርዳል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ይገመግማል፣

39.9 ከዞን ከብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር አኳያ የሚኖሩ የአሠራር መመሪያዎችን አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ ከክልሉ የሥራ አመራር ቦርድጋር በመነጋገር እንዲወጣለት ያደርጋል፤

39.10 የሥራ አመራር ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ከሁለት ጊዜ ተከታታይ የምርጫ ዘመን ሊበልጥ አይችልም፡፡

## 40. የኮሚቴው የስብሰባ ሥነ-ስርዓት

40.1 ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ያደርጋል፤

40.2 አስቸኳይ ስብሰባ በፕሬዘዳንቷ ወይም ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት 1/3ኛው ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል፤

40.3 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ምልዐተ-ጉባኤ ከአባላቱ 50%+1 የተገኙበት ይሆናል፤

40.4 ውሳኔዎችም በስብሰባው ላይ በተገኙ 50+1 አባላት ድምጽ የሚተላለፉ ሲሆን፤ የጉባኤተኞች ድምፅ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ በጉባኤዉ ሰብሳቢ የተደገፈው ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፤ ለምክር ቤቱ መወያያ አጀንዳ ያዘጋጃል፤

40.5 ጉባዔው አንድን ጉዳይ ባብላጫ ድምጽ በሚወስንበት ጊዜ ሁሉ የአነስተኛው ድምጽ አስተያየት በስብሰባው ቃለ-ጉባዔ መመዝገብ ይኖርበታል፤

40.6 የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የራሱን ዝርዝር ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርአት ማስፈጸሚያ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 41. የስራ አመራር ቦርድ ፕሬዘዳንቷ ተግባርና ሃላፊነት

ሰብሳቢዋ በዚህ ሕገ-ደንብ አንቀጽ 27.3 መሠረት ከዞኑ /ከብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም ከሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች ተመርጣ የሥራ የስራ አመራር ቦርድ አባል በመሆኗ የዞኑ /የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩ ፕሬዘዳንት ሆና የምታገለግል ሲሆን፤ ተጠሪነቷም ለክልሉ ምክር ቤት፣ እና ለዞኑ /ለብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም ለሬጂዮ ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩ የሥራ አመራር ቦርድ ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሯታል፦

41.1 የሥራ አመራር ቦርዱን ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ትመራለች፤

41.2 የሥራ አመራር ቦርድ ተግባራትን ታስተባብራለች፣ ውሣኔዎችን ታስፈጽማለች፤

41.3 ማኀበሩን በመወከል ከ3ኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ታደርጋለች፣ ስምምነቶችን ትፈራረማለች፤

41.4 የሥራ ሪፖርትና የስብሰባ አጀንዳ ታዘጋጃለች፣ ታቀርባለች፤

41.5 በዞኑ/በብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም በሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩ ስርለሚገኙ ሠራተኞችና በጎ ፈቃደኞች የሥራ ስምሪት ትሰጣለች፣ ትከታተላለች፣ ትገመግማለች፤

41.6 በተዋረድ ያሉትን የማኅበሩ መዋቅሮች በበላይነት ትመራለች፣ ታስተባብራለች፣ ትከታተላለች፤

41.7 በሥራ አስፈጻሚው የሚሰጣትን ሌሎች ተግባራት ታከናውናለች።

## 42. የምክትል ፕሬዘዳንቷ ተግባርና ሃላፊነት

ከሥራ አመራር ቦረዱ መካከል ተመርጣ ተጠሪነቷ ለፕሬዘዳንቷና ለዋና ለሥራ አመራር ቦርዱ ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሯታል፦

42.1 ፕሬዘዳንቷ በማትኖርበት ወይም ሥራዋን ለማከናወን በማትችልበት ጊዜ ተክታ ትሠራለች፤

42.2 የሚሰጡ ውሳኔዎችንና አቅጣጫዎችን ከሰብሳቢዋ ጋር በመመካከር ታስፈጽማለች፣ ትፈጽማለች፤

42.3 ከፕሬዘዳንቷ ቀጥላ በዞኑ /በብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም በሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩ እና በተዋረድ ያሉ የማኅበሩ ፈጻሚዎችን እቅድ ታወርዳለች፣ ትከታተላለች፣ ትመራለች፤

42.4 የዕቅዶችን አፈጻጸም በመከታተል ሪፖርት ታደርጋለች፤

42.5 በሥራ አመራር ቦርዱና በፕሬዘዳንቷ ተለይቶ የሚሰጣትን ተግባራት ታከናውናለች።

## 43. የማህበሩ የዞን ጽ/ቤት

የማህበሩን የዞን ጽ/ቤት በቋሚነት የሚመሩ አንድ የጽ/ቤት አስተባባሪ እና እንደአስፈላጊነቱ እንደተቋሙ የፋይናንስ አቅም እየታየ ሌሎች የሙያ መደቦች በሰው ሃብት አስተዳደር መመሪያ የሚመለስ ይሆናል።

## 44. የማኅበሩ የዞን /የብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም ሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤት አስተባባሪ /ዳይሬክተር/

የዞን/ብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም ሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤት አስተባባሪ ለሥራ መደቡ የተዘጋጀውን ዝቅተኛ መስፈርት የምታሟላ ሴት በቅጥር ወይም በምደባ የምትመደብ ሲሆን፤ ተጠሪነቷ ለዞን /ለብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም ለሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ

አስተዳደር የሥራ አመራር ቦርድ እና የክልል ጽ/ቤት ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሯታል፦

44.1 የማኅበሩን ሕገ-ደንብ ጠንቅቃ ታውቃለች፤

44.2 ከክልል የሚወርዱ እቅዶችን፣ ውሳኔዎችንና አቅጣጫዎችን ታስተባብራለች ትፈጽማለች፤

44.3 ለዞኑ/ለብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም ሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩ የሥራ ማስኬጃ የሚመደበውን በጀት ለወረዳዎች /የከተማ አስተዳደሮች/ ወይም ክፍለ-ከተሞች በማከፋፈል ሥራ ላይ እንዲውል ታደርጋለች፤

44.4 የክልሉን እቅድ መነሻ በማድረግ የዞኑን /የብሔረ-ሰብ አስተዳደሩን/ ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩን እቅድ ታቅዳለች፣ ለወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ክፍለ-ከተሞች እና ቀበሌዎች ታወርዳለች፣ ትከታተላለች፣ ትደግፋለች፤

44.5 ከክልል የሚላኩ የገቢ ማሰባሰቢያ ደረሰኞችን በሥርዓት ለወረዳዎች፣ ለከተማ አስተዳደሮች፣ ክፍለ-ከተሞች እና ቀበሌዎች ታስረክባለች፣ በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውንና የማኅበሩ ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ትቆጣጠራለች፤

44.6 አባላት ያለባቸውን ችግር እያጠናች ችግሩን በማስወገድ ታጠናክራለች፣ የአባላትን ወቅታዊ መረጃ ትከታተላለች፤

44.7 አባላቱማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ በሆኑ ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትቀሰቅሳለች፣ መረጃዎች ትይዛለች፤

44.8 የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በየወቅቱ ለክልሉ ጽህፈት ቤት ትልካለች፣ የክልሉ ጽህፈት ቤት ለሚጠይቀው መረጃ ምላሽ ትሰጣለች፤

44.9 ከአጋር ሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ሴቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ከስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢዋ በሚሰጣት ተልዕኮ በቅንጅትና በትብብር ትሰራለች፣ ለማኅበሩ የሚሆን ድጋፍ ታፈላልጋለች፤

44.10 በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር እና በክፍለ-ከተማ የሚመደቡ አስተባባሪዎችን በተገቢዉ መንገድ ትመራለች፣ ታስተባብራለች፣ ያሉበትን ትከታተላለች ችግር ሲኖርም የእርምት እርምጃ ትወስዳለች፤

44.11 ከክልል ጽህፈት ቤት እና ከዞን/ከብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም ሬጂዮ-ፖሊታን የሥራ አመራር ቦርድ አባላት እና ከሰብሳቢዋ የሚሰጧትን ሌሎች ተግባራት ታከናውናለች፡፡

44.12 የእቅድ እና ፕሮግራም ባለሞያው ተግባርና ሃላፊነት በሰው ሃብት አስተዳደር መመሪያው ይመለሳል፡፡

## 45. የዞን /የብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ

45.1 ብዛታቸው ሶስት አባላት የሚገኙበት እንደአግባቡ የዞን /የብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚቴ በዚህ ሕገ-ደንብ ተቋቁሟል፤

45.2 የኮሚቴው ተጠሪነት እንደአግባቡ ለዞኑ /ለብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም ለሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩ የሴቶች ማኅበር ስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ይሆናል፤

45.3 በዚህ ሕገ-ደንብ አንቀጽ 26 ለክልሉ የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚሽን የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደአግባቡ ለዞኑ /ብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ወይም የሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 46. የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ አማራ ሴቶች ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ

46.1 እንደአግባቡ የወረዳው ወይም የከተማ አስተዳደሩ ወይም የክፍለ-ከተማው ሴቶች ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ የሚቋቋመው ከየቀበሌው በማኅበሩ አባላት በተመረጡ የጉባኤ አባላት ሲሆን፤ የወረዳው ወይም የከተማ አስተዳደሩ ወይም የክፍለ-ከተማው ሴቶች ማኅበር ከፍተኛ አካል ነው፤

46.2 የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ ጠቅላላ ጉባዔ በዚሁ ሕገ-ደንብ አንቀጽ 19-21 ለክልል ጠቅላላ ጉባኤ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር እንደአግባብነቱ ይዞ ይሠራል።

## 47. ስለወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ ምክር ቤት አመራረጥ እና አሠራር

47.1 የወረዳው ምክር ቤትበወረዳው ስር ካሉ ሁሉም ቀበሌዎች በቀበሌ አንድ ሴትን በመምረጥ የሚቋቋም ይሆናል፤

47.2 የምክር ቤቱ አባላት ስብሰባ በ6 ወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል፤

47.3 አስቸኳይ ስብሰባ በሊቀ-መንበሯ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት 1/3ኛው ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል፤

47.4 ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የምክር ቤት አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፤

47.5 ውሳኔዎችም በስብሰባው ላይ በተገኙ 50+1 የምክር ቤቱ አባላት ድምጽ የሚተላለፉ ሲሆን፤ የተሰብሳቢዎች ድምፅ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ በምክር ቤቱ ሰብሳቢ የተደገፈው ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፤

47.6 ምክር ቤቱ አንድን ጉዳይ ባብላጫ ድምጽ በሚወስንበት ጊዜ ሁሉ የአነስተኛው ድምጽ አስተያየት በስብሰባው ቃለ-ጉባዔ መመዝገብ ይኖርበታል፤

47.7 የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የራሱን ዝርዝር ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርአት ማስፈጸሚያ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 48. የምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነቶች

48.1 እንደአግባቡ የወረዳውን ወይም የከተማ አስተዳደሩን ወይም የክፍለ-ከተማውንሴቶች ማኅበር እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፤

48.2 የጉባኤው ውሣኔዎችና ዓላማዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ክትትል ያደርጋል፤

48.3 ሴቶች በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ተሳታፊ እንዲሆኑ ያነሳሳል፤

48.4 የማኅበሩን ገንዘብና ንብረት ይቆጣጠራል፣ ከክልል በቀመር የሚላክለትን በጀትና እቅድ ደልድሎ ያፀድቃል፤

48.5 የምክር ቤቱን ውሳኔዎችና የውይይት ሂደቶች በቃለ-ጉባኤ ተይዘው በቀጣዩ መደበኛ ስብሰባ እንዲጸድቁያደርጋል፤

48.6 የተለያዩ ጥፋቶችን የፈጸሙና ሥራቸውን በአግባቡ ያላከናወኑ የምክር ቤቱ እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ከሥራቸው ያሰናብታል፤

48.7 የማኅበሩ የሂሳብ አሠራር በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፤

48.8 እንደአግባቡ በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ ወይም በክፍለ-ከተማው የሚካሄዱ የገቢ ማስገኛ ተግባራትን እየገመገመ ይመራል፡፡

## 49. የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደሩ ወይም የክፍለ-ከተማው የሥራ አመራርቦርድተግባር እና ኃላፊነቶች

49.1 ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በምክር ቤቱ አባላት የሚመረጡ ብዛታቸው ከ5 - 7የሆኑ እንደአግባቡ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ የሥራ አስፈጻሚ አመራር ቦርድ አባላት የሚኖሩት ራሱን የቻለ አካል በዚህ ሕገ-ደንብ ተቋቁሟል፤

49.2 የኮሚቴው ተጠሪነት እንደአግባቡ ለወረዳው ወይም ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

ሀ) በውስጡ የሥራ ክፍፍል ያደርጋል፣

ለ) የሥራ ሪፖርት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

ሐ) በክልሉ ምክር ቤት የፀደቁ የተለያዩ መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

መ) በተዋረድ የሚገኙ የማኅበሩን መዋቅሮች የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

ሠ) እንደአግባቡ ከዞን /ከብሔረ-ሰብ አስተዳደር /ወይም ከሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር የሚወርዱ እቅዶችን፣ ውሳኔዎችንና አቅጣጫዎችን ያስፈጽማል፣

ረ) የማኅበሩ አባላት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚያካሂዱት የልማት እንቅስቃሴዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማነሳሳትና በማሳመን ይሠራል፣

ሰ) የሴቶችን የእኩልነት መርህ የሚቃረኑ፣ የበታችነት፣ ያለዕድሜ ጋብቻንና ሌሎች ኋላቀር ድርጊቶች እንዲቀረፉ ይታገላል፣

ሸ) የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎ እንዲያድግ ይሠራል፣

ቀ) ነባር የማኅበሩ አባላትን ያጠናክራል፣ አዳዲስ አባላት ወደ ማኅበሩ እንዲገቡ ይሰራል፣

በ) የማኅበሩ አባላት የተለያዩ ሙያዊ ስልጠናዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስተባብራል፣ ከስልጠናው በኂላ ያለውን ሂደትም ይከታተላል፣ ሪፖርት ያደርጋል፣

ተ) የስነ-ምግባር ጉድለት በሚያሳዩ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ላይ በ2/3ኛ ድምጽ ሲወሰን ከኃላፊነታቸው ያግዳል፣

ቸ) በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ ተ) ድንጋጌ መሠረት ከአባልነት የታገደች የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የተወሰነባት ውሳኔ አግባብነት የለውም ብላ ካመነች ቅሬታዋን አዘጋጅታእንደ አግባቡ ለወረዳው ወይም ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለክፍለ-ከተማው የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ማቅረብ ትችላለች፣

ኀ) በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ ቸ) መሠረት የወረዳው ወይም የከተማ አስተዳደሩ ወይም የክፍለ-ከተማው የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚቴ የሰጠው ውሳኔ ያላረካት እንደሆነ ቅሬታዋን አዘጋጅታ ለክልሉየኦዲት እና ቁጥጥር ኮሚሽን ማቅረብ ትችላለች፣

ነ) ከቀበሌስራ አመራር ቦርድ ጋር በየሩብ ዓመቱ ስብሰባ ያደርጋል፣

ኘ) የማኅበሩ የገቢ ምንጭ እንዲያድግ ቀበሌዎችን በማስተባበር የወር ክፍያና ሌሎች ገቢዎች ይሰበስባል፣

አ) ለተለያዩሥራዎች ማስፈፀሚያ ተብሎ ለወረዳዎች ወይም ለከተማ አስተዳደሮች ወይም

ለክፍለ-ከተሞች የሚመደብ በጀትን በተገቢ ሁኔታ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ለዞን /ብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም ለሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ለወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ ምክር ቤት የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፤

49.3 የማኅበሩ ሥራ አመራር ቦርድ አባላት ሆነው የሚመረጡ ተመራጮች ለሴቶች ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ የኢኮኖሚ ፤ የማህበራዊ፤ መልካም አስተዳደርና ውሳኔ ሰጭ ከሆኑ ተቋማት የሚገኙ ጠንካራ ሴቶች ፤ በሴትነት ጾታቸው ከተደራጁ ሲቪክ ማህበራት ፤ተጽኖ ፈጣሪ ከሆኑ ሴቶች እንዲሁም በጉባዔ ከተመረጡ የምክር ቤት አባላት ሆኖከመንግሥትም ሆነ ከፖለቲካ ፓርቲ ተሿሚነት ነፃ የሆኑና በሌላ አቻ አደረጃጀት ውስጥ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ያልሆኑ መሆን አለባቸው፤

49.4 የሥራአመራር ቦርድ አባላትየሥራ ዘመን ከሁለት ጊዜ ተከታታይ የምርጫ ዘመን ሊበልጥ አይችልም፡፡

## 50. የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ አማራ ሴቶች ማኅበር ስራ አመራር ቦርድ ፕሬዘዳንት

እንደአግባቡ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ ሴቶች ማኅበር ስራ አመራር ቦርድፕሬዘዳንት ተጠሪነቷ ለወረዳው ወይም ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለክፍለ-ከተማው የማህበሩ ምክር ቤት እና ለዞኑ /ብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ/ ወይም ሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደሩ ሴቶች ማኅበር ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ታከናውናለች፡-

50.1 የማኅበሩን ሕገ-ደንብ ጠንቅቃ በማወቅ እንደአግባቡ የወረዳውን ወይም ከተማ አስተዳደሩን ወይም ክፍለ-ከተማውን ሥራ በኃላፊነት ትመራለች፣ ትቆጣጠራለች፤

50.2 ስለማኅበሩ የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተከታትላ ትፈጽማለች፣ በወቅቱ ሪፖርት ታደርጋለች፤

50.3 የወረዳውን ወይም የከተማ አስተዳደሩን ወይም የክፍለ-ከተማውን እና የቀበሌዎችን ሥራ በበላይነት ትመራለች፣ ታስተባብራለች፣ ትከታተላለች፤

50.4 ለቀበሌዎች ድጋፍ ታደርጋለች፣ የተጓደሉ የሥራ አመራሮች እንዲተኩ ታደርጋለች፤

50.5 ከዞን /ከብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም ከሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር የሚላክላትን ዕቅድ መነሻ በማድረግ እንደአግባቡ የወረዳውን ወይም የከተማ አስተዳደሩን ወይም የክፍለ-ከተማውን ዕቅድ ታወጣለች፣ የወጣውን ዕቅድ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲሠራበት ክትትል ታደርጋለች፤

50.6 ከክልል እና ከዞን /ከብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም ከሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር የሚላኩ የገቢ ማሰባሰቢያ ደረሰኞችን ለቀበሌዎች ታስረክባለች፣ በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውንም ትቆጣጠራለች፣ የገቢ አሰባሰብና የገንዘብ አላላክ በመመሪያው መሠረት መፈፀሙን ትከታተላለች፤

50.7 ከክልል እና ከዞን /ብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም ከሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር የሚላከውን በጀት በትክክል ስራ ላይ ታውላለች፣ ሂሳቡንም ወቅቱን ጠብቆ መወራረዱን ትከታተላለች፡፡

50.8 ሌሎች በምክር ቤቱ እና በሥራ አመራር ቦርዱየሚሰጧትን ተግባራት ታከናውናለች፡፡

## 51. የምክትል ፕሬዘዳንቷ ተግባርና ሃላፊነት

ከሥራ አመራር ቦረዱ መካከል ተመርጣ ተጠሪነቷ ለፕሬዘዳንቷ ለዋና ለሥራ አመራር ቦርዱ ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሯታል፦

51.1 ፕሬዘዳንቷ በማትኖርበት ወይም ሥራዋን ለማከናወን በማትችልበት ጊዜ ተክታ ትሠራለች፤

51.2 የሚሰጡ ውሳኔዎችንና አቅጣጫዎችን ከፕሬዘዳንቷ ጋር በመመካከር ታስፈጽማለች፣ ትፈጽማለች፤

51.3 ፕሬዘዳንቷ ቀጥላ በወረዳ ወይም ክፍለ ከተማ እና በተዋረድ ያሉ የማኅበሩ ፈጻሚዎችን እቅድ ታወርዳለች፣ ትከታተላለች፣ ትመራለች፤

51.4 የዕቅዶችን አፈጻጸም በመከታተል ሪፖርት ታደርጋለች፤

51.5 በሥራአመራር ቦርዱና ፕሬዘዳንቷተለይቶ የሚሰጣትን ተግባራት ታከናውናለች፡፡

## 52. የማህበሩ የወረዳ /ከተማ አስተዳደር /ክፍለ ከተማ/ ጽ/ቤት

የማህበሩን የወረዳ/ ከተማ አስተዳደር / ክፍለ ከተማ/ ጽ/ቤት በቋሚነት የምትመራ አንድ የጽ/ቤት ሐስተባባሪ ይኖረዋል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ እንደተቋሙ የፋይናንስ አቅም እየታየ ሌሎች የሙያ መደቦች በሰው ሃብት አስተዳደር መመሪያ የሚመለስ ይሆናል ፡፡

የወረዳ /ከተማ አስተዳደር /ክፍለ ከተማ/ ጽ/ቤት አስተባባሪ /ዳይሬክተር/ ለሥራ መደቡ የተዘጋጀውን ዝቅተኛ መስፈርት የምታሟላ ሴት በቅጥር ወይም በምደባ የምትመደብ ሲሆን፤ ተጠሪነቷ ለወረዳ /ከተማ አስተዳደር/ክፍለ ከተማ/ የሥራ አመራር ቦርድ እና የዞን ጽ/ቤት ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሯታል፦

52.1 ከክልል እና ከዞን /ብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም ከሬጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር የሚላከውን በጀት በትክክል ስራ ላይ ታውላለች፣ ሂሳቡንም ወቅቱን ጠብቆ እንዲወራረድ ታደርጋለች፤

52.2 አባላት ያለባቸውን ችግር እያጠናች ችግሩን በማስወገድ ታጠናክራለች፣ የአባላትን ወቅታዊ መረጃዎችን ትይዛለች፣ መረጃ የሚጠይቁ ክፍሎች ሲጠይቁ ትሰጣለች፤

52.3 አባላቱ ማኀበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ በሆኑ ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትቀሰቅሳለች፣ መረጃዎችን ትይዛለች፤

52.4 ከአጋር ሴክተር መሥሪያ ቤቶች እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ሴቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች በቅንጅትና በትብብር ትሠራለች፣ ለማኀበሩ የሚሆን ድጋፍ ታፈላልጋለች፤

52.5 በስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢና እና በሥራ አመራር ቦርዱ አባላትየሚሰጧትን ተግባራት ታከናውናለች፡

## 53. የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ

53.1 ብዛታቸው ሶስት አባላት የሚገኙበት እንደአግባቡ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚቴ በዚህ ሕገ-ደንብ ተቋቁሟል፤

53.2 የኮሚቴው ተጠሪነት እንደአግባቡ ለወረዳው ወይም ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለክፍለ-ከተማው የሴቶች ማኀበር የስራ አመራር ቦርድ ይሆናል፤

53.3 በዚህ ሕገ-ደንብ አንቀጽ 26 ለክልሉ የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚሽን የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደአግባቡ በወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 54. የቀበሌ ሴቶች ማኀበር ጠቅላላ ጉባኤ፣

54.1 የቀበሌጠቅላላ ጉባኤ የማኀበሩ አባላት የሆኑ የቀበሌውን ነዋሪ ሴቶች በሙሉ በአባልነት የያዘ የቀበሌ የሴቶች ማኀበር ከፍተኛ ውሳኔ ሰጭ አካል ነው፤

54.2 የቀበሌው ምልዐተ-ጉባኤ በዚሁ ሕገ-ደንብ አንቀጽ 19-21 ለክልሉ ጠቅላላ ጉባኤ የተሰጡትን ሥልጣን እና ተግባር እንደ አግባብነቱ ይዞ ይሠራል።

## 55. የቀበሌ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

በምርጫ የተወከሉ ብዛታቸው ከ45 የማያንሱ አባላትን የያዘ የቀበሌው ሴቶች ማኀበር ምክር ቤት ተቋቋመ ሲሆን ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

55.1 የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ይመርጣል፤

55.2 እንደአግባቡ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ-ከተማ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የፀደቁ ሥራዎችን ያስፈጽማል፤

55.3 የማኅበሩን አባላት በማሳመን በተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

55.4 በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ የሐይል ጥቃቶችን ለማስቀረት ይታገላል፤

55.5 በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ የተለያዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በተለይም ያለ እድሜ ጋብቻ እንዳይፈፀም የማሳመን እና የመከላከል ሥራዎችን ይሠራል፣ያስተምራል፤

55.6 የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሣደግ ሴቶች በየደረጃው ባሉ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያነሳሳል፣ ያሳምናል፤

55.7 አዳዲስ አባላትን ያፈራል፣ ነባሮችን ያጠናክራል፤

55.8 የማኅበሩ አባላት በተለያዩ የሙያ ስልጠናዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይመለምላል፣ እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፣ ከስልጠና በኋላም ስላመጡት ለውጥ ይከታተላል፤

55.9 ሴቶችና ህፃናት የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይቀሰቅሳል፤

55.10 በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ በብዛትና በጥራት እንዲያድግ ጥረት ያደርጋል፤

55.11 ሁለንተናዊ የሴቶች ተሳትፎን የሚቃረኑ ሥራዎች ሲሠሩ በመቃወም እንዲስተካከሉም ጥረት ያደርጋል፡፡

## 56. የምክር ቤቱ የስብሰባ ሥነ-ስርዐት

56.1 ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባውን በሶስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል፤

56.2 አስቸኳይ ስብሰባ በሊቀ-መንበሯ ወይም ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት 1/3ኛው ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል፤

56.3 የምክር ቤቱ ምልዐተ-ጉባኤ ከአባላቱ 50%+1 የተገኙበት ይሆናል፤

56.4 ውሳኔዎችም በስብሰባው ላይ በተገኙ 50+1 አባላት ድምጽ የሚተላለፉ ሲሆን፤ የተሰብሳቢዎች ድምፅ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ በጉባኤዉ ሰብሳቢ የተደገፈው ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፤

56.5 ምክር ቤቱ አንድን ጉዳይ ባብላጫ ድምጽ በሚወስንበት ጊዜ ሁሉ የአነስተኛው ድምጽ አስተያየት በስብሰባው ቃለ-ጉባዔ መመዝገብ ይኖርበታል፤

56.6 የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የራሱን ዝርዝር ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርአት ማስፈጸሚያ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 57. የቀበሌ ሥራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

57.1 ብዛታቸው አምስት አባላትን የያዘ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጥ ተጠሪነቱ ለቀበሌ ምክር ቤት የሆነ የሥራ አመራር ቦርድ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተቋቁሟል፤

57.2 በውስጡ የሥራ ክፍፍል ያደርጋል፤

57.3 ለምክር ቤቱ የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፤

57.4 የስነ-ምግባር ጉድለት ያሳየች የሥራ አመራር ቦርድ አባልን በ2/3ኛ ድምጽ ከቀበሌ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት እንድትሰናበት የሚጠይቅ የውሳኔ ሀሳብ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፤

57.5 የቀበሌውን የሴቶች ማኅበር በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ጎጦችን በመከፋፈል ይደግፋል፤

57.6 በቀበሌ ምክር ቤት የተቀመጡትን የሥራ ክፍሎች በበላይነት ይመራል፣ ይሠራል፤

57.7 ከአባላት የሚሰበሰብ ወርሃዊ ክፍያን በጊዜው ይሰበስባል፤ በወቅት ወደ ወረዳ ገቢ ያደርጋል፡፡

57.8 የቀበሌ ምክር ቤቱን ስብሰባና የማኅበሩን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፡፡

## 58. የቀበሌ ሥራ አመራ ቦርድ የስብሰባ ሥነ-ስርዓት

58.1 ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ያደርጋል፤

58.2 አስቸኳይ ስብሰባ በኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት 1/3ኛው ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል፤

58.3 የሥራ አመራ ቦርዱ ምልዐተ-ጉባኤ ከአባላቱ 50%+1 የተገኙበት ይሆናል፤

58.4 ውሳኔዎችም በስብሰባው ላይ በተገኙ 50+1 አባላት ድምጽ የሚተላለፉ ሲሆን፤ የተሰብሳቢዎች ድምፅ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ በሰብሳቢዋ የተደገፈው ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፤

58.5 ኮሚቴው አንድን ጉዳይ ባብላጫ ድምጽ በሚወስንበት ጊዜ ሁሉ የአነስተኛው ድምጽ አስተያየት በስብሰባው ቃለ-ጉባዔ መመዝገብ ይኖርበታል፤

58.6 የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የራሱን ዝርዝር ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርአት ማስፈጸሚያ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 59. የቀበሌ ሴቶች ማኅበር የስራ አመራር ቦርድ ፕሬዘዳንት

የቀበሌ ሴቶች ማኅበር የስራ አመራር ቦርድ ፕሬዘዳንት ተጠሪነቷ ለቀበሌው ሴቶች ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ፤ምክር ቤት እና እንደአግባቡ ለወረዳው ወይም ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለክፍለ-ከተማው ሴቶች ማኅበር ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ታከናውናለች፡-

59.1 የማኅበሩን ሕገ-ደንብ ጠንቅቃ በማወቅ የቀበሌውን ሥራ በኃላፊነት ትመራለች፣ ትቆጣጠራለች፤

59.2 ስለማኅበሩ የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተከታትላ ትፈጽማለች፣ በወቅቱ ሪፖርት ታደርጋለች፤

59.3 የቀበሌዎችን ሥራ በበላይነት ትመራለች፣ ታስተባብራለች፣ ትከታተላለች፤

59.4 ለኅጦች ድጋፍ ታደርጋለች፣ የተጓደሉ የሥራ አመራሮች እንዲተኩ ታደርጋለች፤

59.5 እንደአግባቡ ከወረዳ ወይም ከከተማ አስተዳደር ወይም ከክፍለ-ከተማ የሚላክላትን ዕቅድ መነሻ በማድረግ የቀበሌውን ዕቅድ ታወጣለች፣ የወጣውን ዕቅድ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲሠራበት ክትትል ታደርጋለች፤

59.6 ከክልል፣ ከዞን /ከብሔረ-ሰብ አስተዳደር/ ወይም ከሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር እና እንደአግባቡ ከወረዳ ወይም ከከተማ አስተዳደር ወይም ከክፍለ-ከተማ አስተዳደር የሚላኩ የገቢ ማሰባሰቢያ ደረሰኞች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ትቆጣጠራለች፣ የገቢ አሰባሰብና የገንዘብ አላላክ በመመሪያው መሠረት መፈፀሙን ትከታተላለች፤

59.7 አባላት ያለባቸውን ችግር እያጠናች ችግሩን በማስወገድ ታጠናክራለች፣ የአባላትን ወቅታዊ መረጃዎችን ትይዛለች፣ መረጃ የሚጠይቁ ክፍሎች ሲጠይቁ ትሰጣለች፤

59.8 አባላቱ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ በሆኑ ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትቀሰቅሳለች፣ መረጃዎችን ትይዛለች፤

59.9 ከአጋር ሴክተር መሥሪያ ቤቶች እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ሴቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች በቅንጅትና በትብብር ትሠራለች፣ ለማኅበሩ የሚሆን ድጋፍ ታፈላልጋለች፤ ለሌሎች የስራ አመራር ቦርድ አባላት ስራ አከፋፍላ ትሰጣለች፤ የስራ አፈጻጸሙን ትገመግማለች።

59.10 ሌሎች በምክር ቤቱ እና ሥራ አመራር ቦርዱ የሚሰጧትን ተግባራት ታከናውናለች።

## 60. የቀበሌ ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ

60.1 ብዛታቸው ሶስት አባላት የሚገኙበት የቀበሌ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ በዚህ ሕገ-ደንብ ተቋቁሟል፤

60.2 የኮሚቴው ተጠሪነት ለቀበሌው የማኅበሩ የስራ አመራር ቦርድ ፕሬዘዳንት ይሆናል፤

60.3 በዚህ ሕገ-ደንብ አንቀጽ 26 መሠረት ለክልሉ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደአግባቡ በቀበሌ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴም ተፈጻሚ ይሆናል።

## 61. የማኅበሩ የፋይናንስ  አሰራር፣ የሰው ሃብት አስተዳደርና የንብረት አያያዝ

61.1 ማህበሩ ካለፉት ስርዓተ መንግስትና በዚህ ስርዓተ መንግስት የተረከባቸው ለረጅም ጊዜ ሲያስተዳድራቸውና ሲጠቀምባቸው የቆዩ ልዩ ልዩ ሃብቶችን (የእርሻ መሬት፤ የከተማ ቦታና ቤት፤ ወፍጮ ቤቶች ደን  ወዘተ… ) የሚመነጨውን ገቢ ከብክነት ለመታደግ በክልል ጽ/ቤት በሚከፈት አካውንት ገቢ እየተደረገ በአንድ ቋት ይተዳደራል፡፡ ማንኛውም በየደረጃው ያለ የማህበሩ መዋቅር ወደክልል የልዩ ልዩ ሃብት አካውንት ገቢ ያደረገውን ገንዘብ የፕሮጀክት  እቅድ በማውጣት በማኅበሩ ሥራ አመራር ቦርድ ወይም የጽ/ቤቱ አመራሮች እየታየ ተቀባይነት ሲያገኝ የተለያዩ ለማህበሩ ስራ ያውላል፡፡ የአፈጻጸም ዝርዝር መመሪያ ይወጣለታል፡፡

61.2 የማኅበሩ የፋይናንስ አሠራር ሥርአት፣ የሰው ሃብት አስተዳደር፣ የማኅበሩ የንብረት አስተዳደር እና የአመራሮች ጥቅማጥቅም በመመሪያ እንዲመለስ የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 62. ሕገ-ደንቡን ስለማሻሻል

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በማንኛውም አግባብ በተጠራ የጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ወይም ልዩ አብላጫ ድምጽ ውሳኔ ሊሻሻል፣ ሊከለስ ወይም ሊሻር ይችላል፡፡

## 63. መተዳደሪያ ሕገ-ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላጉ ባኤው ተሻሽሎ ከጸደቀበት ከግንቦት 25 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡